## ዓለም አቀፍ የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር

## Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization

**P.O.Box 703913 , Dallas ,TX 75370-3913**

**USA Tel 469 432 2435**





*ቀን 03/21/2015*

- *ለተባበሩት የአሜሪካ መንግሥት ፕሬዚዳንት የተከበሩ ባራክ ኦባማ*
- *ለሮማው ጳጳፅ ቅዱስ ፍራንሲስ*
- *ለካናዳ ጠቅላይ ሚኒስትር ለኩቡር ስቴፈን ግሬት*
- *ለታላቅዋ ቢሪታኒያ ጠቅላይ ሚኒስትር ለኩቡር ዴቪድ ካሜሮን*
- *ለጀርመን ቻንስለር ለክብርት አንጀላ ሜርከል*
- *ለፈረንሳይ ፕሬዝዳንት ለኩቡር ፍራንኮይስ ሆላንዴ*
- *ለአውስትራሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር ለኩቡር ቶኒይ አቦት*
- *ለሲዊዲን ጠቅላይ ሚኒስትር ለኩቡር ስቴፋን ሎፍቬን*
- *ለተባበሩት የአሜሪካ መንግሥታት ምክትል ፕሬዝዳንት ለኩቡር ጆ ባይድን*
- *ለተባበሩት የአሜሪካ መንግስት የውጪጉዳይ ጸሃፊ ለኩቡር ጆን ኬሪ*
- *ለተባበሩት የአለም መንግስታት ዋና ጸሐፊ ለኩቡር ባን ኪ ሙን*
- *ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ለክብሪት ዶር ኒኮሳዛና ደላሚኒ ዞማ*
- *ለተባበሩት የአሜሪካ ሴናተር ለኩቡር ጆን ሚኬይን*
- *ለዓለም ቀይ መስቀል*
- *ለተባበሩት መንግሥታት ስደተኞች ክፍል ኮሚሽነር*
- *ለዓለም የወንጀል ችሎት*
- *ለሰው መብት ተመልካቾች*
- *ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል*

*በመጀመሪያ ይህን ደብዳቤ ለመጻፍ እድሉን ስላገኘን ምስጋናችንን እያቀረብንልዎት , የእኛን የቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎችና የፖሊስ ሰራዊት አለምአቀፍ ማህበር ችግሮችን ወደ እርስዎ ስናቀርብ መፍትሔ እንደምናገኝና የእኛንም ፍላጐት ወደ ግባችን እንደምናደርስ በመተማመን ነው።*

*ጉዳዩም--*

*1, በህገ ወጥ መንገድ በፈረሰዉ የቀድሞዉ የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎችና የፖሊስ ሰራዊት አባላት ላይ ስለሚፈጸመዉ የሰብአዊ መብት ጥሰትና ኢሰብአዊ ድርጊት ፤*

ዓለም አቀፍ የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር

**Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization**

**P.O.Box 703913 , Dallas ,TX 75370-3913**

**USA Tel 469 432 2435**




*2, በስደት ከአፍሪካና ከመካከለኛዉ ምስራቅ ከሚገኙ አባሎቻችን ስለቀረበዉ የአስቸኳይ ድረሱልን ጥያቄ በሚመለከት*

*ክቡርነትዎ*

*ክቡርነትዎ እንደሚያዉቁት በማንኛዉም ሃገር የአንድ ሃገር መከላከያ ሰራዊት ከህብረተሰቡ የወጣና የህብረተሰቡ አካል ሲሆን ዓላማዉ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ባለበትም ሆነ በሌለበት ሀገር ከየትኛዉም የፖለቲካ ፓርቲ ሳይወጣ በገለልተኝነት የሃገሩን ዳር ድንበር , የአየር ክልልና የባህር በር ማስከበር ነዉ።*

*በሃገራችን በኢትዮጵያም እንደማንኛዉም ሃገር የመከላከያ ሰራዊት የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በዘመናዊ መንገድ በ1927 እ,ኤ,አ ከተቋቋመበት ግዜ ጀምሮ በህገወጥ መንገድ በ1983 እ,ኤ,አ በአሁኑ የኢትዮጵያ መንግስት እስከፈረሰበት ድረስ ላለፉት ሰማንያ አመታት ይህንኑ በማንኛዉም ሃገር የሚሰራበትን መርህ አድርጎ ቀደም ሲል በነበሩት የተለያዩ የኢትዮጵያ መንግስታት ስር በመሆን እናት ሃገራችንን ከዉጪ ወራሪና ከዉስጥ ተገንጣዮችና ሽብር ፈጣሪዎች ስንከላከልና የአግራችንን ጥቅም ስናስከብር ፤ ከዚያም አልፎ በተባበሩት መንግስታት አዛዥነት በደቡብ ኮርያና ኮንጎ አለም አቀፍ ግዳጃችንን ስንወጣ እንደነበር ይታወቃል።*

*ይሁን እንጂ በ1983 እ,ኤ,አ የወታደራዊዉ መንግስት ከስልጣን ከተወገደ በኋላ በምትኩ የመጣዉ የአሁኑ መንግስት በማንኛዉም ሃገር ባልታየና ባልተደረገ ሁኔታ ይህንን ከሰማንያ አመታት በላይ ያስቆጠረ ከትዉልድ ወደትዉልድ እየተከታተለ የሃግራችንን ብሄራዊ ደህንነትና ጥቅም ሲያስከብር የነበረ ወደ ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጉ የሰራዊቱ አባላትን ከነቤተሰቡ እንደጠላት ጦር በመመልከት አንድ መንግስት ነኝ የሚል ኃይል በማይፈጽመዉ ሁኔታ ይህንን ብሄራዊ የመከላከያ ሰራዊት በማፍረስና በመበተን ፤ እነዚህን በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሃገራቸዉን ያገለገሉ የሰራዊቱ አባላት በማሰር ፤ በመግደል እንዲሰደዱና በማንኛዉም ቦታ ተቀጥረዉ እንዳይሰሩ በማድረግ ፤ ምንም እንኳን ከቅጥር እስከ ሰራዊቱ መፍረስ ድረስ ለብዙ ዓመታት የጡረታ ታክሳቸዉን ሲከፍሉ ቢኖሩም የጡረታ መብታቸዉን በመከልከል ፤ ብሎም ያለምንም ካሳ በማሰናበት ከነቤተሰቡ ቤት አልባ አድርገዉ ፤ በረንዳ አዳሪ በማድረግ ፤ ከፊሉንም ለብዙ ዓመታት አስሮ በማሰቃየት፤ ለግማሾቹ ደግሞ ህይወታችዉን እንዲያጠፉ ምክንያት በመሆን፤ የአዕምሮ በሽተኛ እንዲሆኑ ፤ ቤተሰቦቻቸዉም በረሃብና በችግር እንዲያልቁ ፤ የቀሩትም በአፍሪካና በመካከለኛ ምስራቅ በስደት እንዲሰቃዩ አድርገዋል።*

*የሀገሪቱንም ሉዑላዊነት ለማስከበር ሲሉ የአካል ጉዳት የደረሰባቸዉን የሰራዊቱን አባላት ይረዱና ያገግሙበት ከነበረዉ የማገገሚያ ማዕከል በኢሰባዊነት ሙሉ በሙሉ ማዕከሉን በመዝጋት እነዚህን የአካል ጉዳተኛ የሰራዊቱ አባላት ከማዕከሉ እንዲባረሩ በማድረግ ብዙዎች እርዳታ እንዳያገኙ በመደረጉ ምክንያት ህይወታቸዉ ሲያልፍ ቀሪዎቹ ደግሞ በልመና ስራ ላይ ተሰማርተዉ አሰቃቂ ኑሮ እንዲኖሩ ተገደዋል።*

*ከዚህም በተጨማሪ አሁን በስልጣን ላይ ያለዉ የኢትዮጵያ መንግስት ኢትዮጵያን ፤ የአሁኑ የኤርትራ መንግስት ኤርትራን ከተቆጣጠሩ በኋላ ጦርነቱ ስለአበቃ በጄነቫ ስምምነት መሰረት የእስረኛ ልዉዉጥ በሁለቱ ሀገር መካከል መደረግ ሲገባዉ ፤ የኢትዮጵያ መንግስት በኢትዮጵያ በኩል ተማርከዉ የነበሩ የኤርትራ ምርኮኞች ሙሉ በሙሉ ለኤርትራ*

Email (feafww@gmail.com) website (www.formerethiopianarmedforceworldwide.org)

ዓለም አቀፍ የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር

**Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization**

**P.O.Box 703913 , Dallas ,TX 75370-3913**

**USA Tel 469 432 2435**

*ሲያስረክቡ , በተመሳሳይ ሁኔታም ኤርትራ ዉስጥ ያሉት የተማረኩትም ይሁን በፈቃደኝነት ከአለቆቻቸዉ በተሰጣቸዉ ትዕዛዝ መሰረት መሳሪያቸዉን ያስቀመጡትን ከ60 ሺህ በላይ የሚሆኑ የመከላከያ ሰራዊት አባላት(ሌላዉ ቀርቶ ሲቪሎችም ሳይቀር) በተመሳሳይ ሁኔታ ጦርነቱ ስለአለቀ በጄኔቫ ዉል መሰረት (ምንም እንኳ ኤርትራ ዉሉን ባትፈርምም) በሰብአዊነት እንዲለቀቁ በኢትዮጵያ መንግስት ምንም አይነት ጥረትም ሆነ ፍላጎት ሳያሳይ በመቅረቱ እነዚህ ከ60 ሺህ በላይ የሆኑ የመከላከያ ሰራዊት አባሎቻችን ላለፉት 23ዓመታት በኤርትራ መንግስት እጅ ሆነዉ በየትኛዉም ሀገር በ21ኛዉ ክፍለ ዘመን ሊታሰብ በማይገባ ሁኔታ፣ እነዚህ ዜጎቻችን በኤርትራ በረሃ ላይ ዛሬም በአሰቃቂ ሁኔታ በመከራና ሲቃይ እንዲሞቱ ፤ የአእምሮ በሽተኛ እንዲሆኑ ፣ ልሳናቸዉን እንዲያጡ ፣ የኤርትራ ሰልጣኝ ሰራዊት ዒላማ መለማመጃ እንዲሆኑ፣ የበረሃ መንገድ ስራተኛና የከባድ ጉልበት ሰራተኛ ባሪያ እንዲሆኑ አድርገዋቸል። ይህ ወንጀል እስከ አሁንዋ ደቂቃ ድረስ እየተከናወነ ይገኛል።*

*ይህንንም ጉዳይ በተመለከተ የእኛ ድርጅት ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያንና የኤርትራን መንግስት ጠይቆ ምንም ምላሽ ያላገኘን ሲሆን ይህንኑ የኤርትራ መንግስት ኢሰብአዊ ወንጀልና ድርጊት ዓለም እንዲያዉቀዉ በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ምንም ሙከራ ወይም ጥረት ሳያደርግ እንዲያዉም ምንም እንደማያዉቅና ምንም እንደሌለ መስለዉ ተባባሪ ሆነዉ ይገኛሉ። በዓለም ታሪክ የአንድ ሀገር መንግስት ነኝ፤ ለዜጎች ደህንነት እቆማለሁ እያለ ከ60 ሺህ በላይ ዜጎቹ በጠላት ኃይል ተይዘዉ ሲሞቱ ፣ ሲሰቃዩ የሚያይ መንግስት ነኝ የሚል ኃይል ቢኖር ያለዉ በኢትዮጵያ ብቻ ነዉ።በሶማሊያ ወረራና ጦርነት*

*ከዚህ መከራና ሲቃይ ያመለጥነዉ ጥቂት ዕድለኞች የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኮሚሽን ፣የተባበሩት የአሜሪካ መንግስት ፣ የካናዳ መንግስት ፣ የታላቋ ብሪታንያ መንግስት፣ የአዉስትራሊያ መንግስት፣ የሲዉዲን መንግስት፣ የጀርመን መንግስት ወዘተ,,,,,, በሱዳን ፣በጁቡቲ፣በኬንያ ፣ በጣሊያን ፤ በግሪክ፣በየመን፤ ወዘተ,,,,,,በኩል በሰብዓዊነት በአበረጉልን እርዳታ ዕድሉን ተጠቅመን እነሆ ዛሬ ብዙዎቻችን ከላይ በጠቀስናቸዉ ሀገሮች ቤተሰብ አፍርተን የሰላም አየር እየተነፈስን ሰብዓዊ መብቶቻችን ተከብሮ የየአለንበት ሀገር ዜጋ ጭምር ሆነን ወልደን ከብረን በያለንበት ሀገር የህብረተሰቡ አካል በመሆን ለአለንበትም ህብረተሰብ ገንቢ አስተዋፅዖ እያደረግን እንገኛለን።*

*ክቡርነትዎ*

*ለዚህም ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ለተባበሩት መንግስታት ድርጂት ፤ ለተባበሩት መንግስታት የስደተኖች ኮሚሽን ፤ ለተባበሩት የአሜሪካ መንግስት ፤ ለካናዳ መንግስት፤ ለአዉስትራሊያ መንግስት ፤ ለሲዊድን መንግስት ፤ ለጀርመን መንግስት ፤ ለታላቋ ብሪታኒያ መንግስት ወዘተ,,,, ለስደተኛ ወገኖቻችን ላደረጉት አስተዋጽኦ ያለንን ከልብ የመነጨ አክብሮትና አድናቆት ብሎም ምስጋና ጭምር ለማቅረብ እንወዳለን።*

*ክቡርነትዎ*

*በአሁኑ ሰዓት በስደት ላይ ያሉ የቀድሞዉ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት አባላት መከራና ሲቃይ የቀጠለ ሲሆን፤ በተለይ በአፍሪካና በመካከለኛዉ ምስራቅ በተለይ በሱዳን፤በጁቡቲ፤በኬንያ፤በሊቢያ ፤ በየመንና በሳዉዲ ዐረብያ*

Email (feafww@gmail.com) website (www.formerethiopianarmedforceworldwide.org)

ዓለም አቀፍ  የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር

**Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization**

**P.O.Box  703913 , Dallas ,TX 75370-3913**

**USA    Tel 469 432 2435**



*ያሉት የቀድሞ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እጅግ በጣም ለህይወታቸዉ አስጊ  በሆነ ሁኔታ ላይ ያሉ ስለሆነ እነዚህን ሁሉ ችግሮች ከግምት ዉስጥ በማስገባት ክቡርነትዎ፤*

*1ኛ, ሁሉንም ለጊዜዉ ባይቻል እጅግ ለህይወታቸዉ በጣም አሳሳቢ የሆነ ሁኔታ ለገጠማቸዉ በተለይ በኢትዮጵያ መንግስት ከላይ በጠቀስናቸዉ የጎረቤት ሀገሮች ጋር በመነጋገርም ይሁን በህገወጥ መንግድ አፍኖ ለመዉሰድ አሊያም ለመግደል እያሳደዳቸዉ ሲሆን እነኚህ አባሎቻችንም ከቦታ ወደቦታ በመሯሯጥ አደገኛ ሁኔታ ሁኔታ ላይ ያሉትን ጥቂቱን ህይወታቸዉን ለማትረፍ እንችል ዘንድ የአስቸኳይ የድረሱልን ጥያቄዎች ያቀረቡልንና እኛም አጣርተን ያረጋገጥነዉ በጣም ጥቂቶቹን ሀገርዎና መንግስትዎ እነዚህን የሀገራቸዉን ብሔራዊ ደህንነትና ሉኡላዊነት እንደ አንድ የመከላከያ ሰራዊት ከማስከበር በስተቀር ምንም ወንጀል የሌለባቸዉ ሰለሆነ እነዚህን የቀድሞ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት አባላትን በአስቸኳይ ቅድሚያ ተሰጥቶአቸዉ ወደ ሶስተኛ ሀገር ተሸጋግረዉ እንደ እኛ የሰላም አየር ለመተንፈስ እንዲችሉ የተለመደዉን  ትብብር መንግስትዎ ያደርግላቸዉ ዘንድ እየጠየቅን ስማቸዉንና ያሉበትን ቦታ በየትኛዉም ግዜ ከተጠየቅን ለማቅረብ ዝግጁ ነን።*

*2ኛ በየትኛዉም የዓለም ሀገር ባልታየና  ሁኔታ ለሀገር ቆሜያለሁ በሚል መንግስት የሃገርን ብሔራዊ መከለከያ ሰራዊት አፍርሶና በትኖ ፤ በህገወጥ መንግድ ለዓመታት የከፈሉትን የጡረታ መብታቸዉን በመከልከል፤ እንዲሁም ሌላም ስራ እንዳይሰሩ አግዶ ለ23 ዓመታት ከነቤተሰቦቻቸዉ በረሃብ፣በስቃይና በቤት አልባነት በመቶ ሺህ የሚቆጠሩትን የቀድሞዉ የመከላከያ ሰራዊት ማሰቃየት ህገወጥ ብቻ ሳይሆን ኢሰብአዊ ተግባር ስለሆነ መንግስትዎ ይህንን ኢሰብአዊና ህገወጥ ድርጊት አዉግዞ ይህም ድርጊት እንዲቆምና የጡረታ መብታቸዉ እንዲከበርና ካሳም እንዲከፈላቸዉ ተጽዕኖ እንዲያደርጉ ያደርጉልን ዘንድ፤*

*3,ኛ የትዉልድ ሀገራችንን ብሄራዊ ደህንነትና ጥቅም ለማስከበር በተደረገዉ ጦርነት የአካል ጉዳት ደርሶባቸዉ በተቋቋመዉ የጀግኖች አምባ የማገገሚያ ማዕከል ሲረዱ የነበሩትን የቀድሞዉ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት አባላት በኢሰባዊነት ከማዕከሉ አስገድዶ በማስወጣትና ማዕከሉንም በመዝጋት በተፈጸመዉ ህገወጥ ወንጀል የተነሳ አብዛኛዎቹ የሚያስፈልጋቸዉን ዕርዳታ ባለማግኘታቸዉና የሚያገኙትም ዕርዳታ ሙሉ በሙሉ በመቋረጡ ህይወታቸዉ ያለፈ ሲሆን በህይወት የቀሩት ጥቂቶችም በስቃይና በልመና በበረንዳ አዳሪነት እየተሰቃዩ ስለሆነ የእርስዎም መንግስት ይህንን ኢሰብአዊ ድርጊት አዉግዞ ለሞቱት ቤተሰቦቻቸዉ ካሳ እንዲከፍሉ አሁን በህይወት ላሉት የጡረታ መብታቸዉ ተከብሮ ከሳ እንዲሰጣቸዉ እንዲሁም ወደ ማዕከሉ እንዲመለሱ ተፅዕኖ እንዲያደረጉ ይረዱ ዘንድ፤*

*4ኛ, በኤርትራ በመጭረሻዋ ደቂቃ በአለቆቻቸዉ ትዕዛዝ በሰላም እጃቸዉን ሰጥተዉም ሆነ በምርኮኝነት ያሉትን የቀድሞዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባሎችን የኤርትራ መንግስት ለመስማትና ለማመን በሚከብድ ሁኔታ ለ23 ዓመታት እየፈጸመ ያለዉን ኢ,ሰብዓዊ  ተግባር የእርስዎ መንግስት እንዲያወግዘዉና እነዚህ ዜጎቻችንን ለማስፈታት እንዲሁም በአለም ቀይ መስቀል እዉቅና አግኝተዉ አስቸኳይ እርድታ እንዲያገኙ  መንግስትዎ የበኩሉን ተፅዕኖ እንዲያደርግ ይረዱን ዘንድ ፤*

ዓለም አቀፍ  የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ማሕበር

**Former Ethiopian Armed Forces Worldwide Organization**

**P.O.Box  703913 , Dallas ,TX 75370-3913**

**USA    Tel 469 432 2435**

*5ኛ,በኢትዮጵያም  መንግስት በግፍ ታስረዉ ያለ ፍርድ እስከዛሬ ድረስ እየተሰቃዩ ያሉትን የቀድሞዉ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ላይ የሚፈጸመዉን የእስራት ፤የግርፋት አሰቃይቶ የመግደልን  ኢሰብአዊ ድርጊት መንግስትዎ እንዲያወግዝና እንዲለቀቁም ተጽዕኖ ያደርጉልን ዘንድ እንዲሁም  የአሁኑ የኢትዮጵያ መንግስት ስልጣን በያዘ ማግስት ባለስልጣኖቹ  ያለአግባብ ስልጣናቸዉን በመጠቀም የቀድሞዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላትን በአደባባይ ያለምንም የፍርድቤት ዉሳኔ በገዛ ፈቃዳቸዉ በማሰር ፣ በመግረፍ እንዲሁም በመረሸን ወንጀል የፈጸሙ የስርአቱ ባለ ስልጣናትና ግለሰቦች ለአለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ መንግስትዎ ተጽዕኖ ያደርጉ ዘንድ በታላቅ ትህትና እንጠይቃለን።*

*የቀድሞዉ የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎችና የፖሊስ ስራዊት አለምአቀፍ ማህበር*

*ሊቀመንበር*

ashebr gebre

*አሸብር ገብሬ*

*ግልባጭ*

- *ለጠቅላይ ሚኒስትር አቶ  ኃይለማርያም ደሳለኝ*

*የኢትዮጵያ ፌደራል ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር*

*አዲስ አበባ*

- *ለፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ*

*የኤርትራ መንግሥት ፕሬዚዳንት*

*አስመራ*